# የወቅቱ የኢትዮጵያ የፖለቲካ÷ ማህበራዊ÷ ኢኮኖሚያዊ÷ ዲፕሎማሲያዊና ሌሎችም ተዛማጅ ሁኔታዎች

## ክፍል ሶስት

በክፍል ሁለት ዝግጅታችን ምንም እንኳን ዛሬ ከህወሓት/ኢህአዴግና ከደጋፊዎቻቸዉ ጋር እየተፋለመ ያለዉ መጠነ ሰፊ የሆነው የሕዝባችን ክፍል ቢሆንም÷ በዚህ ጎራ የተካተቱ የኅብረተሰብ ክፍሎችና የፖለቲካ ሃይሎች በሙሉ ወጥነት ያለዉ አመለካከት ተመሣሣይ ጥቅምና ፍላጎት ወይም አንድ ዓይነት ራዕይ ያላቸዉ እንዳይደሉ በመጠቆም ነበር የደመደምነው። የሕወኃት/ኢሕአዴግን ልዩ ልዩ መልኮች የመገምገማችንን ያሕል ራሳችንንም መለስ ብሎ መመልከቱ ለወደፊት እንደሚበጅ በተለይም ከሕዝብ የወገኑ ናቸው የሚባሉቱ ኅብረቶች ጠንካራና ደካማ ጎኖችን በሰፊው ለመመርመር ቃል ገብተን ነበር የተለያየነው የዛሬው ዝግጅታችን በዚሁ ጉዳይ ላይ ነው የሚያተኩረው።

ልዩነቶቻቸዉን አዉቀዉና አቻችለዉ ነገር ግን የጋራ ጠላታቸዉ የሆነዉን÷ ህዝቡንና ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችን እየጨቆነ እየበደለና እየተጋፋ ያለዉን÷ በኢትዮጵያ ዉስጥ ብቸኛ ባለሥልጣንና ገዥ የሆነዉን ህወሓት/ኢህአዴግን በኅብረት በመታገል ለመጣልና ከሥልጣን ለማስወገድ ነበር ከሶስት ዓመት በፊት የተስማሙት - በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ጥላ ስር የተሰባሰቡት ድርጅቶች ዋና ዓላማ ::

ከሐምሌ 19 ቀን እስከ ሐምሌ 26 ቀን 1995 ዓ.ም. በሮክቪል ከተማ ሜሪላንድ ዉስጥ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)ን ሲመሠርቱ ሁሉም መሥራች የነበሩት የፖለቲካ ድርጅቶች÷ ሁሉም በጋራ የሚጠይቋቸዉ መሰረታዊ ነገሮች ነበሩ:: ከነዚህም ዉስጥ ዋነኞቹና ቀዳሚዎቹ የዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ÷የዜግነት መብት መከበር÷ ሃሣብን በነጻነት የመግለጥ መብት÷ የመሰብሰብ መብት÷ የመደራጀት መብት÷ እንዲሁም የመምረጥና የመመረጥ መብት ተጠቃሾች ናቸው።

ኢሕአፓ የሰው ልጅ የተሟላ ሰብዕናውን ለማግኘት እንዲችል÷ የዕድገት ክብረወሰንንም ለመቀዳጀት ነፃነት ያስፈልገዋልና ኢትዮጵያውያንም ነፃነት ሊኖራቸው ይገባል ብሎ በፅኑ ያምናል:: ኢትዮጵያ ዉስጥ የሕዝቡ ባለቤትነትና ባለሙሉ ሥልጣን መሆን መረጋገጥ አለበት:: ይህ የሕዝቡ ባለሙሉ ሥልጣንነት (ሶቨርኒቲ) ደግሞ ከሞላ ጎደልም ቢሆን ሊረጋገጥ የሚችለዉ መሠረተ ሰፊ ዴሞክራሲ በሀገራችን ዉስጥ ሊተከልና ሊጸድቅም ሲችል ነዉ::የኢትዮጵያ ሕዝብ መሠረታዊ ነጻነቶች ሊከበሩ ይገባል ስንል ወይንም መሠረተ-ሠፊ ዴሞክራሲ ስንል፡ ዴሞክራሲ ከንድፈ ሃሳብ ባሻገር

በተጨባጩ እንዲለመልምና እንዲሰራበት ማለታችን ነው። በዝርዝር ለመተንተን ያሕል፥
(ሀ) ዴሞክራሲ እንደ መንግሥት ሥርዓት ሊቋቋም ወይንም ሊመሠረት ይገባል፥
(ለ) ዴሞክራሲ በዘርፈ ብዙ የሕግ ዋስትና የሚኖራቸዉ ተቋሞች መኖር አማካይነትም ሕልውናውን ሊያበስር ይገባል፤ በሲቪክ ማኅበሮችና በነፃ ጋዜጦች(ኢንስቲቱሽንስ) መስፋፋትና፥ ሥር መስደድ ይገለጣል፥
(ሐ) ዴሞክራሲ እንደ ተለምዶአዊ ባህልና እሴት (ባህልና በጎ ምግባር) ሊለመድና ሊወሰድም ይገባል።

የሰብዓዊ መብቶች መከበር ስንልም ሀገራችን የሁሉም ኢትዮጵያዊ ሕይወት የሚከበርባት ሀገር ትሁን፤ ሌሎችም መብቶች/ነጻነቶች ይከበሩ፥ የዕምነት ነፃነት ይኑር፥ የመንቀሳቀስ ነፃነት፥ መኖሪያ ሥፍራን የመምረጥ ነፃነት፥ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በመረጠው ሥራ የመሥራት ነፃነት ይኑረው ማለታችን ነው።

የሕግ የበላይነት በተግባር ይረጋገጥ ስንልም፥ የፍርድ ቤቶች ነፃነት ይረጋገጥ፥ ያለፍርድቤት ትዕዛዝ ዜጎች አይታሠሩ ማለታችን ነው።
ዴሞክራሲ ሊሠፋና ሊበለጽግ የሚችል ፖለቲካዊ ፅንሠሃሣብ ቢሆንም ዛሬ ባለበት ደረጃ የተሟላ አይደለምና በዚሁ ተግባራዊ እየሆነ ባለበት ክልል የአብዛኛው ክፍል ሃሣብ የበላይነት ቢይዝም የዉሁዳንን ሃሣብ በማክበር ከአድላዊነትና ከጉዳት ከለላ መስጠት ደግሞ ግድ ይላል፤
ልዩነቶችን በጸጋ መቀበልና ማስተናገድ፥እንዲሁም መቻቻል ሌላው የዴሞክራሲ ገፅታ ነው።

ዴሞክራሲ መሠረቱ ሊሰፋና ስር ሊሰድ የሚችለዉ ደግሞ ከላይ በመሪዎች ስለታወጀ ወይንም በየተወሰኑ ዓመቶች የምርጫ ትርዒት ለሕዝብ በመቅረቡ ሣይሆን ለሚመለከተዉ ሕዝብ ማኅበራዊ ፍትኅ የማስገኛ መርሆዎችንና ፖሊሶዎችን ሲያካትት ነዉ። ዴሞክራሲ የማኅበራዊ ፍትኅ ገፅታዎቹን እያጣ ከመጣ በርግጥም ጫጭቷል ኮስምኗል ማለት ይቻላል።

ከአንድ ሀገር ሕዝብ በርከት ያለዉ ክፍል በደዌ ሲሰቃይ በህመም ሲደቅ በተስቦና ቀሣፊ በሽታዎች ሲያልቅ አቅም ያለዉና በሕዝብ ይሁንታ የሚቋቋመዉ መንግሥት ዝም ብሎ የሚመለከት ከሆነ “የሕዝብ አገዛዝ”የሚለዉ ቃል ትርጉም የለሽ ነዉ የሚሆነዉ። በዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ የማንኛውም ዜጋ ሕይወት ዋስትና ሊያገኝ ይገባል እንላለን።

አሁንም የሀገርና የሕዝብ ተስፋ የሆኑት ሕጻናት በምግብ በተለይም ለዕድገታቸዉ አስፈላጊ በሆነዉ በአልሚ ምግብ፥ በክትባት በመድኃኒት በህክምና እጦት በሕጻናትና በልጅነት ሲያልቁ የማዳንና የሕይወት ዋስትናን የመስጠት ኃላፊነት የማይወስድ ዴሞክራሲያዊ ነኝ የሚል መንግሥት ሕዝባዊነቱ አጠራጣሪ ስለሚሆን የዚህ ዓይነቱን መንግሥት

የዴሞክራሲያዊነት ካባ ማልበስ ከለበጣ አነጋገርና አጭበርባሪነት አያልፍም፡፡

ትምህርትና የዕዉቀት መስፋፋት በአጠቃላይ ለሰዉ ልጅ ዕድገትና መሻሻል ቁልፍ በሆኑበት፥ ዓለም በቴክኖሎጂ ዕድገት እሽቅድድም ዉስጥ ገብቶ አንደኛዉ ሀገር ሌላኛውን ለመብለጥ በሚዉተረረተርበት ዘመን፥ትምህርትን ዕድሜአቸዉ ለሚፈቅድላቸዉ ወጣቶችና ጎልማሳዎች በነጻ ለመስጠት የማይችል መንግሥት ዴሞክራሲያዊ ነኝ ቢል ስያሜዉ ከግብሩ ጋር መጣጣሙ ያጠራጥራል፡፡

ዴሞክራሲያዊ መንግሥት የሕዝቡን በችጋር መቆላትና በጠኔ ማለቅ የሕዝቡን መጠለያ ማጣትና የበርካታ ወጣቶችንም በጎዳና ተዳዳሪነት የሚቃወምና ሁኔታዉን ለመለወጥም ተግቶ የሚሠራ መሆን አለበት፡፡የአንድ ዜጋ መብት መሠረታዊም ሆነ ሌላ በሕግ ካልተረጋገጠ በሕግ አስፈጻሚዉ ክፍል ዕዉቅናና ተከባሪነትን ካላገኘ በዚሁ ክፍል ካልተጠበቀ/ካልተከበረ መብት አለ መባሉ ትርጉም አይኖረዉም፡፡ሕግ ደግሞ ገዢዎች ተገዢዎችን “ጸጥና ለጥ” አድርገዉ የሚገዙበት እንዳፈቀዳቸዉ ተገዢዉን ሕዝብ አገልጋያቸዉና መሣሪያቸዉ የሚያደርጉበት ከሆነ የዴሞክራሲያዊ መንግስት ህግ ወይንም በሕዝቡ ይሁንታን ያገኘ ሕግ ሊሆን አይችልም፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ለእኒህ ጉዳዮች መሟላት እንታገላለን፥ ለዚህም ነው የተቋቋምነው የሚሉ የተደራጁ ኃይሎች እንደመኖራቸው ቁጥራቸውም መጠነ ሰፊ ከሆነ ሰነበተ ቀረብ ብለን ስንመለከት ማኅበራዊ ፍትህን ያካተተ ሠፊና በሕዝባዊ መርሆዎች ላይ የተመሰረቱ ዴሞክራሲን የሚሹ እንደ ኢህአፓ ያሉት ኃይሎች በዚሁ በተቃዋሚ ጎራ ዉስጥ አሉ፡፡ የዚያኑ ያሕል ስለዴሞክራሲ ያላቸዉ አመለካከት እንደ መንግሥታዊ ሥርዓት (ምርጫን፥ የሥልጣን ክፍፍልን) ከያዙና መንግሥታዊ ሥርአቱም የተለመዱትን የዴሞክራሲ ተቋሞችንም ከያዘ ሊያረካቸዉ የሚችሉም መኖራቸዉ እሙን ነዉ፡፡

ራሳቸዉ የሥልጣን ኮርቻን ካገኙ ሊበቃቸዉ የሚችሉም ለመኖራቸው አጠያያቂ ሊሆን አይችልም፡፡ ጥቅማቸዉን ሊጠብቁበት፥ የበላይነትንም ሊጨብጡበት የሚፈቅድ ወይም አጋጣሚ የሚፈጥርላቸዉ፥ ዴሞክራሲያዊ ሊባል የሚችል ሥርዓት ለማምጣት የሚሹ አሁን ባለው ሁኔታ ግን ከሠፊው ሕዝብ ጎንና አብረውም እየታገሉ ያሉ ይኖራሉም ብለን እንገምታለን፡፡
በተቃዋሚነት ከተሰለፈዉ ሠፊ ክፍል ዉስጥ በብሔረሰብ ወይም በክልል ተደራጅተዉ ይታገሉ የነበሩ ኃይሎች ዉስጥ ብቻም ሳይሆን በርዕዮተ ዓለማዊና በአስተሳሰብ ደረጃ ቢሆን ለ“አንድ ሰዉ አንድ ድምጽ” ከሚባለዉ ለየት ባለ “የቡድን/የኅብረተሰብ መብቶችንም” ክብደት ሰጥቶ ማስተናገድን አጽንዖት የሚሰጡ እንዳሉም መገመት አዳጋች አይሆንም፡፡ ይህኛዉ

አስተሳሰብ ከጠባብ ብሔረተኛነት ወይም ከትላልቅ ብሔሮች ትምክህተኛነት የተለየና ትክክለኛ ምላሽንም የሚጠይቅ ነዉ::
በሀገራችን ዉስጥ የሚመሠረተዉ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እስከዛሬ ሀገሪቱን ዘላቂ ሰላም የነሣትን የብሔረሰቦችን ጥያቄ በትክክል ወይም አርኪ በሆነ ደረጃ መመለስ ስላለበት እንደ ኢህአፓ ያሉ ሃይሎች የሕዝቡን እኩልነት ፌዴራላዊ አስተዳደርን እንደ አማራጭ የመፍትሔ መንገድ ሲያቀርቡ ቆይተዋል::

ምን ዓይነት ፌዴራላዊ ሥርዓት የሚለዉን በተመለከተ በርካታ መዘዞችን ያስከተለ የብሔሮች ወይም የዘውጌ ፌደሬሽን ንድፈ ሃሳብ የሚተካ ሌሎችንም መስፈርቶች ባካተቱ ጥናቶች ላይ የሚመሰረት ወደፊት በሕዝቡ ተመራጮች የሚወሰን አማራጭ ማስፈለጉ በኢሕአፓ ይታመንበታል:: በድርጅቶች የተለያዩ አማራጮች ከነጥናታቸው ሊቀርቡ ቢችሉም የሚወሰነዉ ግን ሕዝቡ ራሱ በሚመርጣቸዉ ተወካዮቹ ቢሆን የተሻለ ተቀባይነት ይኖረዋል፥ በዴሞክራሲያዊ መንገድም የሚወሰን ይሆናል:: ዛሬ በሀገራችን ዉስጥ ያለዉን ገና ያልለየለት የፍጥጫና የተፋፋመ ትግል እንዲሁም የከፍተኛ ዉጥረት ሁናቴ ስንመለከት አያሌ አሳሳቢ ነገሮች እንዳሉ እንረዳለን::
ኢህአፓ በኢዴኃን ዉስጥ በኅብረት ግንባር አባልነቱ ሕጋዊ ሆነዉ በሀገር ዉስጥ በሚሠሩት ድርጅቶች አማካይነት ሊያደርግ የሚችለዉን ሁሉ እያደረገ ነበር -እስተቅርብ ጊዜ ድረስ የቆየው::
ኢዴኃን ግን ኢህአፓን ተክቶም ሆነ እንደኢህአፓ ሆኖ ሊሠራለት አይችልም::ስለዚህም ኢህአፓ በህገወጥነት ተፈርጆ እሀገር ዉስጥ በኅቡዕ እየሠራ ባለበት ሁኔታ ተሣትፎዉንና ሚናዉን ሁናቴዎቹ ይገቱበታል::
ከህብረት ግንባር ባህሪ በሚመነጩ መርሆዎች ተገዝቶ በአንድ በኩል የሚያምንባቸዉን ሃሣቦች፥አመለካከቶች በማቅረብ ለማሳመንና ተቀባይነት አግኝተዉ በኅብረት ግንባሩ አማካይነት እንዲሰራባቸዉ ለማድረግ እየጣረ በጋራ የሚታመንባቸዉን ጉዳዮች/ፖሊሲዎች ከሌሎቹ ጋር እያራመደ፥ ሌሎቹም አክብረው እስከሄዱበት ወቅት ድረስ፥ የሚለይባቸዉን ደግሞ ኅብረቱን በማያናጋ መንገድ ለመግለጽ እየጣረ ነበር የሠራው::
አስቸጋሪ ሁናቴዎችና የማይዘለሉ ተግባሮች ግን ዛሬ እንደገና የመፍትሔ ያለህ እያሉ በርግጥም ከፊታችን ተደቅነዋል::

ቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ህወሓት/ኢህአዴግ ሥልጣን ከያዘ በኋላ እሀገር ዉስጥ ተመስርተዉ በህጋዊነት የሚሰሩ የተወሰኑ የፖለቲካ ድርጅቶችንና ሌሎችንም በቅርቡ ከዉስጥም ከዉጭም የተሰበሰቡ ቡድኖችን ያካተተ ኅብረት/ጥምረት ነዉ:: ነባሮቹ የቅንጅት አባል ድርጅቶች በፊት ኢዴኃን ሲመሠረት አባላቱ የነበሩ የኢዴኃንን የፖለቲካ ፕሮግራም መተክሎችና ፖሊሲዎች የተቀበሉ ነበሩ::
የመላ ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በመባል የሚታወቀዉንና ዛሬ ኢዴአፓ/መድኅን እየተባለ የሚጠራዉ ቡድን በተለያዩና ተመሣሣይነት

ባላቸዉም ምክንያቶቻቸዉ ከኢድኃን በመዉጣት ከሌሎች አዲስ ቡድኖች ጋር ሆነዉ በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ተሰባሰቡ።
እዚህ ላይ መኢአድና ኢዴአፓ በህብረት ዉስጥ እያሉ ያነሷቸዉን አንዳንድ ነጥቦች ለታሪክ ማስታወሻነት ለማንሳት እንገደዳለን፥ ከኅብረት ምሥረታዉ በፊት የፖለቲካ ድርጅቶች ዉህደትን እንጂ ኅብረትን አንደግፍም የሚል ሃሳብ በመኢአድ ይቀነቀንና ይገፋ ነበር።
ኢዴአፓ የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት በጠላትነት እንዳይፈረጅ የመከላከል ጥረት ያደርግ ነበር በኢዴኃን ጉባኤም ላይ ይህንኑ እንደገና አንስቶ አንፀባርቋል። ከዚያም ከሰላማዊ ትግል ዉጭ ምንም ሌላ ዓይነት የትግል ሥልት እንደማያስፈልግ አበክሮ መከራከሩን ቀጠለ- ኢዴአፓ
መኢአድ በኢዴኃን መሥራች ጉባኤ ላይ በተወሰኑት መሠረታዊ የፕሮግራም ነጥቦች ላይ ሙሉ በሙሉ ተስማምቶ ነበር ጉባዔዉ የተጠናቀቀዉ። ምናልባትም የኅብረቱን አመራር ለመሠየም በተደረገው ምርጫ የቁንጮነት ሥፍራ የመኢአዱ መሪ አለመያዝ አስከፍቷቸዉ ካልሆነ በስተቀር አጠንክረዉ የተቃወሙት ዓቢይ ጉዳይ አልነበረም።ኢዴአፓም ቢሆን በጉባዔዉ መጀመሪያ ላይ በብዙ ጥያቄዎች ላይ ልዩነቶችን ጎላ አድርጎ ቢገልጽም በአጠቃላይ ሕዝቡ የኅብረትን ትግልን አጥብቆ እንደሚደግፍ በመገንዘቡ መሠናክል ለመሆን ቢሞክር ራሱን ከሕዝቡ ጭምር የሚነጥል መሆኑን በመረዳት የአብዛኛዉን ሀሳብ ወደ መደገፉ እያደላ መጥቶ ነበር።

ኢዴአፓ አክሮ ልዩነቱን በመግፋት የተሸነፈበት አንዱ ጉዳይ በምርጫ መሳተፍን፥ወደ ምርጫ በተናጠል መግባትና መሳተፍን፥ ለምርጫ ዉድድሩ ሲካሄዱ እያንዳንዱ የኅብረቱ አባል ድርጅት የየራሱን የፖለቲካ ፕሮግራም ይዞ መቅረብ አለበት እንጂ የኅብረቱን የጋራ ፕላትፎርም (የምርጫ ፕሮግራም)ይዞ መወዳደር የለበትም የሚለውን ሃሣብ አጠንክሮ በመግፋት ነበር። ኢዴአፓ በተናጠል መጓዝን፥ አባል ድርጅቶች የየራሳቸዉ የፖለቲካ ፕሮግራሞች ይዘዉ ይቅረቡ የሚለዉን ሃሣብ በመደገፍ ሲከራከር በጉዳዩ ጠቃሚነት አምኖበት ወይንስ ከሌላ ምክንያት ተነስቶ ነበር ኢዴአፓ የተሚገተዉ? ከወደፊቱ አኳያ በኅብረት መቆምን ለምን አጥብቆ ተቃወመው? ብሎ መጠየቅ አግባብ ይኖረዋል። በተለይ ዛሬ ከመኢአድ ጋር የነበረዉንና ያለዉን ልዩነት አስመልክቶ ኢዴአፓ የሚሰጣቸዉ ምክንያቶች ይህን የብቻ ሩጫዉን መላ ያጠናክራል።

ኢሕአፓ እንደሚታወቀዉ ዛሬ የመንግሥት ሥልጣን የጨበጠዉ ህወሓት/ኢህአዴግና በተቃዋሚነት የተሰለፉት የፖለቲካ ድርጅቶች በአቻነት ማለትም በተስተካከለ የዉድድር መስክ ላይ ሊወዳደሩ/ሊፎካከሩ ካልቻሉ በሌላ አነጋገር ኢትዮጵያ ዉስጥ የሚደረገዉ ምርጫ ፍትሃዊ ርትዓዊና ግልጽነት ባለዉ መንገድ የሚካሄድ ካልሆነ ተቃዋሚ ኃይሎች ሊያቸንፉ አይችልም ይል ነበር። ከምንም በፊት አትኩሮት የሰጠዉም እኒህ አስፈላጊ መስፈርቶች እንዲሟሉ ለማድረግ በሚደረገዉ ትግል ላይ ነበር።

ከምርጫው በኋላ ያለው ሁኔታ ዛሬም ከውጥረትና ፍጥጫ አልፎ ወደግጭትም ተለውጦ የበርካታ ኢትዮጵያውያንን ሕይወት መስወዕትነት ጠይቋል፡፡ በጣም በርከት ያሉ በተቃዋሚ ድርጅቶች በተለይም በቅንጅቱ ጥሪ መሠረት እቤታቸው የዋሉ፥ የመኪና ክላስኮችን ያስጮሁ፥ የአደባባይ ሠልፍ የወጡ ወይንም የህወሃት/ኢህአዴግ የፀጥታ ሃይሎች በሚወስዷቸው የሃይል እርምጃዎች ተበሣጭተው ድንጋይ የወረወሩ ዜጎች እንዲሁም በየመንገዱም ሆነ ከመኖሪያ ቤቶቻቸው፥ ከቤተክርስቲያንና ከመስኪድ ታፍሰው የተገደሉም ሲኖሩ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሆኖም ግን አሁን ብዛታቸው ገና በውል ያልታወቀ ዜጎች ተገድለዋል፥ ተደብድበዋል፥ ታስረዋል፥ ቆስለዋል፥ ተሰደዋል፥ ተደብቀዋል፡፡ የሕወኃት/ኢሕአዴግ ጠቅላይ ሚኒስትር ያቋቋመዉ ኮሚሺን እንደዘገበዉ የሟቾች ቁጥር 193 ሲደርስ ቁስለኞችና አካለ ስንኩላን ደግሞ ወደ 1000 ያህል ናቸዉ ፡፡ የሁኔታው አደገኛነት  ለማንም በሚታይ ደረጃ እንደቀጠለ ነው፡፡ የህወሃት/ኢህአዴግ መሪዎች ዕውነተኛውን ባህሪአቸውን፥ አምባገነናዊነታቸውንና አማቂነታቸውን በማያጠራጥር መንገድ ለሁሉምያረጋገጡበት ሁኔታም ተፈጥሮአል፡፡

አሁን ያለው የተፋፋመ ትግል እየተካሄደ ያለበት ሁኔታ በሠፊው ሕዝብ አሸናፊነት ወይንም በድል ካልተጠናቀቀ መጭው ጊዜ ከዚህ በፊት ከነበረው የከፋ የእመቃና
የጭቆና ወቅት ሊሆን እንደሚችል መገመት አዳጋች አይሆንም፡፡ ስለዚህም ሁሉምየሕዝብ ወገን የሆነ ሁሉ ተባብሮና ተረባርቦ ትግሉ እንዲቀጥልና እንዲጠናከር ማድረግ አማራጭ የሌለው ተግባራችን ሊሆን ይገባል፡፡

## <u>የኤርትራ ሁኔታ በቀሪዋ ኢትዮጵያ ላይ ዛሬም መዘዞች ከማስከተል አላቆመም፡፡</u>

ህወሓት/ኢሕአዴግ ያመሠቃቀለው የኤርትራ ጉዳይ የኢትዮጵያን ሀገራዊ ጥቅም በዘላቂ መንገድ በሚያረጋግጥና ሠላም በሚያሰፍን መንገድ ሕዝቦቹን ሙሉ በሙሉ  በማሣተፍ ለመፍታት ተግቶ መሥራት ያስፈልጋል፡፡

ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ የመንግሥት ሥልጣን ጨብጦ ያለው የሕወሓት/ኢሕአዴግ ቡድን በተለይም ጠቅላይ ሚንስትሩ አቶ መለሠ ዜናዊ ከነቡድኑ እስከዛሬ ባሣያቸው ተግባሮቹ ሲመዘን ቢያንስ የኢትዮጵያን ሀገራዊ ሉዓላዊነት ለማስጠበቅ፤ የሕዝቡንና የሀገራችንን መሠረታዊ ጥቅሞች ለመጠበቅ፤ ለማስቀደምና ለማረጋገጥ ተግቶ ሲሠራ አልታየም፡፡ እንዲያውም ተግባሮቹ የሚያሣዩት የኢትዮጵያን ዘላቂ ጥቅሞች የሚጎዱ መሆናቸውን በቀላሉ ለማሳየት ነው የሚቻለው፡፡

ህወሓት ኤርትራን በኢትዮጵያ ተይዛ የነበረች የቅኝ ግዛት ጥያቄ አድርጎ በመውሰድ፣ ለጥቆም ገና ለሥልጣን ሣይበቃ ከዚያን ጊዜ የቃልኪዳን ወዳጁ ከሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ፣ ከሻዓቢያ ፣ጋር በኤርትራ ነፃ መውጣት ጉዳይ ላይ በመስማማት፣ በኋላ ደግሞ ዴሞክራሢያዊ ሁኔታዎች በሌሉበትና ሌሎች አማራጭ ሃሣቦች ሊስተናገዱ በማይችሉበት ሁኔታ "ውሣኔ ሕዝብ" እንዲካሄድ በመተባበርና ውጤቱንም ተቀብሎ በማፅደቅ፣ እተባበሩት መንግሥታት ዘንድም የዕወቁልኝ ጥያቄን በማቅረብ፣ ኤርትራን ለማቋቋምና ለመርዳት ቀሪውን ኢትዮጵያ በመጉዳትና በማራቆት ሲሠራ የቆየ ድርጅት ነው::

ህወሓት ከሕዝባዊ ግንባር ሓርነት ኤርትራ (ሕግሓኤ) ጋር በመመሣጠርና በማሜር ኢትዮጵያን ከዘረፋ ባልተለየ መንገድ እየመዘበረ አዲሲቷን ኤርትራ ለማደርጀትና ለማቋቋም ለአያሌ ዓመቶች ሠርቷል::

በመጨረሻም በአጉል ልማድ እየባለገ የበላይነትም እየተሰማው የመጣውን ሕግሓኤን ከኢትዮጵያ የሚዘርፈውን እንዲቀንስና ሃብትና ጥቅም ማካበት የጀመሩት ሌሎቹም በተለይም በህወሓት ጉያ ውስጥ የተፈጠሩት አዲስ አዳጊ ከበርቴዎች ተራ እንዲያገኙ የተለመዱትን ለሻዓብያ የተመቻቹትን የዝርፊያ ፖሊሲዎችን ለመለወጥ ሙከራዎችና ተግባራዊ ሥምሪቶች ሲጀመሩ ነው በአቶ ኢሣይያስ አፈወርቂ የሚመራው ሕግሓኤ በጠብ መቆራቆስ የጀመረው:: ኤርትራን ሕግሓኤ ብቻውን÷ ቀሪውን የሀገሪቱ ክፍል ግን ሕግሓኤ ከህወሓት ጋር በመጋራት እየመዘበሩ ስለነበረ ሕግሓኤ ይህ የቅምጥል አያያዝ የሚያስገኝለት ከፍተኛ ገቢ እንዳይጓደልበት ሰበቦቹን አፈላልጎ ጠብ ጫረ:: አቶ መለስም የኤርትራ ጥቅም እንዳይቋረጥና ሕግሓኤም እንዳይከፋበት ለማድረግ ተሯሯጠ:: አቶ መለስ ጉዳዩን የኢትዮጵያ ምክር ቤት ለተሰኘው ተቋም እንኳን እንዳያቀርበው በወዳጁ በአቶ ኢሣይያስ ተነግሮት ነበር:: ሆኖም ግን በሻዓብያ ተግባሮችና በአቶ መለስም ልባዊ ትብብር ተመርረው የነበሩትና ለክልላቸው አዲስ በቀል ከበርቴ የቆሙት እነአቶ ሠዬ አብርሃና ገብሩ አሥራት በወቅቱ በእነሱ ይወከል የነበረውን ክፍል ጥቅም አንግበው በመነሣታቸው በህወሓት ውስጥ የበላይነትም ያላቸው መስሏቸው አቋሞቻቸውን አጠንክረው ሊገፉ ቻሉ:: አቶ መለስም ሳይፈልገው ለጊዜውም ቢሆን ኤርትራን ለማጠናከር የተሠማራበትን ተግባሩን የሚያጨናግፍበት ጦርነት ውስጥ ለመግባት ተገደደ::

ከመጀመሪያው የኢትዮጵያን ሀገራዊ ጥቅም በትክክል ሊያስጠብቅ የሚችል የፖለቲካ ድርጅት ኢትዮጵያ ውስጥ የፖለቲካ ሥልጣን ባለመያዙ፣ የህወሓት/ኢሐህአዴግ መንግሥት ለኢትዮጵያ ጥቅም ባለመቆሙ፣ ሁለቱ የቃልኪዳን ወዳጆች በጥቅም ክፍያ እስከተጣሉበት ወቅት ድረስ ከኢትዮጵያ ሕዝብ በስተጀርባ በማሜር÷ ተባብረው እየጨቆኑ፣ እየበደሉና እየመዘበሩም ነበር የቆዩት:: በኋላ ሁለቱ አምባገነናዊ ቡድኖች ተጣልተው የጠባቸውን መንሥዔ እንኳን በውል

ያልተረዳውን ሕዝባችንን ከባድ ጉዳት ወደ አደረሰ ጦርነት ውስጥ አስገቡት:: አቶ መለሰ ዜናዊ በህወሓት ውስጥ የፖለቲካ ተቃዋሚዎቹን ለማዳከምና ለመቆጣጠር እየሠራ በአልጀርስ ስምምነት አማካይነትና ለጥቆም በሄግ ውስጥ የግልግል (የአርቢትሬሽን) ኮሚሽን እንዲቋቋም በመስማማት ለኤርትራ የሚያዳሉትን ግልፅና ሥውር ፍላጎቶቹን በዚሁ ኮሚሽን ውሣኔ መሣሪያነት ለማሟላት ጣረ:: የእነአቶ መለስ ተግባሮች በእርግጥም ብዙ ጥያቄዎችን የሚያስነሱ ናቸው:: ፋርሽ የሆኑ የቅኝ ግዛት ውሎች በማቅረብ ኢትዮጵያ ጨርሶ ለባህር በር እንኳ ህጋዊ ክርክር እንዳታደርግ አገደ ::

አንድ ጊዜ ወደጦርነት ከተገባና ሕዝባችንና ሀገሪቱ ባጠቃላይ ከባድ መሥዋዕት እንዲከፍሉ ከተደረጉ በኋላ ኢትዮጵያውያን በጦርሜዳ ያገኙትን ድል ዘላቂ በሆነ መንገድ የሀገሪቱን ጥቅሞች ለማስጠበቅና በጠላትነት ተሠልፎ የነበረውንም ሃይል በመወጠር ድርድር ራሱ እንዲጠይቅና አንዳንድ ቅድመሁኔታዎችንም እንዲያሟላ በማድረግ ፈንታ ተሽቀዳድሞ ጦርነቱን ማስቆም፣ ጦሩን ወደኋላ እንዲስብ ማድረግ፣ ለጥቆም ጎጂ የሆነውን የአልጀርሱን ውል መፈረም ለምን አስፈለገ? በእነዚህ ርምጃዎች የማንን ጥቅም ነው አቶ መለስ ያስጠበቀው? ያለጥርጥር የኤርትራን ጥቅም ነው ያስጠበቀው::

ለምን ተብሎ ነው ብቃት ያላቸው ኢትዮጵያውያን በብዛት እያሉ በኢትዮጵያ በሚከፈላቸው ባዕዳን ተቀጣሪዎች ሀገሪቱ ተወክላ፣ ሕዝባችን በበቂ ሣያውቀውና ሣይገነዘበው አሁንም ከበስተጀርባው በተውሸለሸለ "አርቢትሬሽን ኮሚሽን" አማካይነት የሚደረስበትን ውሣኔ ገና ከመጀመሪያው "ይግባኝ የሌለው፥ የመጨረሻ ገዥ" አድርጎ የመቀበል ስምምነት የሚደረገው? ለምንስ ተብሎ ነው ኢትዮጵያን በቅኝ ለመያዝ ያካብት የነበረው የፋሽስታዊው የወቅቱ የጣሊያን መንግሥት ያኔ በኢትዮጵያ ገዥዎች ላይ ጭኖት በነበረው ውል ላይ ራሱ ጣሊያን በወራሪነቱ ውሉን ከጣሰውና ዋጋቢስ " ነል ኤንድ ቮይድ" ካደረገው በኋላ የሞተውን፥ ያኔ የቅኝ ገዥ በማስፈራራት የጫነብን ውል ከከርሠ መቃብር ወጥቶ ኤርትራን እንዲያካልል ያስፈለገው?

አብዛኛውን የጦር ሃይሎችን የዕዝ ሠንሠለት በበላይነት የያዙት የቀድሞ የህወሓት ተጋዳዮች የነበሩ ስለሆኑና እነሱ ደግሞ የታገሉለት የክልላቸው መሬት፣ በተለይም ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸው ጋር ሆነው ከባድ መሥዋዕት የከፈሉላቸው የባድመና የሌሎችም አዋሣኝ አካባቢዎች ፣ በኤርትራ መወሰዳቸውን የማይሹ በመሆናቸው፥ በተለይ እነአቶ መለስ የእነዚህን ማለትም ትናንት በመሣሪያ ሃይል ሥልጣን ያስጨበጡትን ክፍሎች ተቃውሞ ሰለሚፈራ ነበር የኮሚሽኑን ውሣኔ በመጀመሪያ "እንደ አንድ ትልቅ የህወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት ድል" አድርገው በማቅረብ በመንግሥት ደረጃ በይፋ የዋሹት:: ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን ዕውነቱን ከሕዝቡ ለመደበቅ የተራወጡት:: በቃላት ዥዋዥዌ እየተጫወቱ

ሲያመነቱና ሁኔታዎቹንም ሲያመቻቹ የቆዩት፡፡ የወሡኑን ጉዳይ በተመለከተ ኤርትራን እስካጠናከረለት ድረስ የኢትዮጵያ መሸራረፍ ለአቶ መለስ እንደማይከፋው ሊያጠራጥረን አይገባም፡፡ በፊትም ሆነ ዛሬ ልቡ ያለው እዚያው ነውና፡፡

ተቃውሞ ሥልጣኑን ሊያሳጣው እንደሚችል በፈራበት ጊዜ፣ በጦርነቱ ማግስት በአንድ ለተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ ነበር አቶ መለስ የኮሚሽኑን ውሣኔ "ለእትዮጵያ ሕዝብ እንዲህ ያለ ግልጽና ዓይን ያወጣ የፍትኅ መጨናገፍን መቀበል ጨርሶ የሚታሰብ አይደለም ብሎ የገለጠው፡፡ አከታትሎም "ስለዚህም ውሣኔው የዘለቄታዊ አለመረጋጋትና ጦርነት ጥንስስ ነው" ያለው፡፡ ውሣኔውን "ሙሉ በሙሉ ሕገ-ወጥ" የሆነና "ተገቢ ያልሆነ" ነው ከማለትም አልፎ ኮሚሽኑን "ሃላፊነት በጎደለው መንገድ በተለይም የባድሜንና የማዕከላዊ ክፍሉን የተመለከተ ውሣኔ ያሣለፈ" ነው በሚል የኮነነው፡፡ አቶ መለስ ይህንን የሄግ ኮሚሽን በሌላም አስገራሚ ጉዳይ ጭምር ከሶት ነበር፡፡ ፋሽሽታዊው የጣልያን መንግሥት ኢትዮጵያን በጦር ሃይል በማጥቃት የቅኝ ግዛቱ ለማድረግ ወረራ ባካሄደበት ወቅት በዚሁ የወረራ ተግባሩ የተነሣ ውድቅ የሆኑትንና÷ የማንኛውም የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚሻ ግለሰብም ሆነ ተቋም መከራከሪያና ማመሣከሪያ ሊሆኑ በማይገባቸው÷ በኢትዮጵያና በኢጣሊያን መሐከል ተደርገው በነበሩ ቅድመ ቅኝ ግዛት "ውሎች ላይ (ወይንም በእንግሊዝኛ ኮሎንያል ትሪቲስ እየተባሉ በሚጠሩት ላይ) "መመሠረት ነበረበት" ውሣኔው ብሎ ነው አቶ መለስ ኮሚሽኑን የወቀሰው፡፡

አቶ መለስ የራሱን ቡድን በማጠናከር የሚቃወሙትንም በበቂ ያዳከመ ሲመስለው በሌላ "ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ" ትርዒት አማካይነት "ባለ አምስት ነጥብ የመፍትሄ ሃሣብ" በሚል በህዳር ወር 1997 ዓ ም መላ-ቅጡ የጠፋ ሠነድ÷ ከዚህ በፊት በይፋ ያወገዘውን የተቃወመውን እግር ከወርች የሚያስር የኮሚሽን ውሣኔ በመቀበል ዓይኖቹን በጨው ያጠበው፡፡ ህወሓት/ኢሕአዴግ በሚቆጣጠረው ምክር ቤት ውስጥ አቶ መለስ ምንም ችግር እንደማይገጥመው ቢታወቅም እስከዛሬ ድረስ ኢትዮጵያን በትክክል ወክሎ የማያውቅ ምክር ቤት ዛሬ ሀገራችንን ከሌላ ሤራ እንዲታደግልን አንጠብቅም፡፡
"አዲስ የሠላም ሥልት" በሚል አቶ መለሡ ዜናዊ በህዳር 1997 ዓ ም ያቀረበው የሃሣብ ድሪቶ ከቃላት ጅዋጅዌ ጨዋታ የዘለለ ምንም አዲስ ቁምነገር አልነበረውም፡፡ ከውጭ የሚያገኘውን÷ ለእሱም እስትንፋስ ሰጪው የሆነውን÷ ርዳታና ብድር እያገኘ እራሱን በሥልጣን ላይ ለማቆየት ሲል የወሰደው እንደልማዱም የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ የሚሰጥ አቋም ነው፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ግልጽ ፍትነዊና ርትዓዊ የሆነ ምርጫ ተካሂዶ በሚመረጥ፣ በርግጥም የኢትዮጵያ ሕዝብን ሊወክል በሚችል፣ ብሔራዊ

ምክር ቤት ውስጥ የኤርትራ ጉዳይ እንደገና መታየት ይኖርበታል ብሎ ያምናል ኢሕአፓ። አሁን ያለው ምክር ቤትም ሆነ የህወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት የኢትዮጵያን ሀገራዊ ሉዓላዊነትና ብሔራዊ ጥቅሞች በተመለከተ ምንም ዓይነት ቋሚ ውሣኔ ለማድረግና ከሌሎች ጋርም "በመደራደር" ስምምነት ላይ ለመድረስ አስተማማኝ ውክልናም ሆነ ብቃት የላቸውም
ኤርትራ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታ በሌለበት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ የተለየ ሃሣብ ያላቸው ኤርትራውያን ሃሣቦች በአቻነት፥ ነፃና ርትዓዊ በሆነ መንገድ ሊገለጹና ሊወዳደሩ በማይችሉበት ሁኔታ በተካሄደ የይስሙልኝ "ውሣኔ-ሕዝብ" (ትርዒት) ኤርትራ እንድትገነጠል መደረጉ የውሣኔውን ዴሞክራሢያዊነት አጠያያቂ አድርጎታል።

ኢሕአፓ ከሰባ ሦስት (73) ሚሊዮን በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደፊት ያለባሕር በር መኖሩ ሊያስከትለው የሚችለውን መዘዝ ትኩረት ሰጥቶ የሚመለከተው መሰረታዊ ጉዳይ ነው። የኢትዮጵያን ጥቅም ለማራመድ የሚመረጥ መንግሥት ኢትዮጵያ ውስጥ ሥልጣን ለመያዝ ከቻለ ያለከባድ ጦርነት ምናልባትም በሠላማዊ ድርድር ሊፈታ የሚችል ነው።

ህወሓት/ኢሕአዴግ የኢትዮጵያን ጥቅም እጠብቃለሁ እያለ፣ ለሕዝባችን እየዋሸ ነገርግን በተከታታይ መብቷን፥ ክብሯንና ጥቅሟንም ጭምር በመሠሪነት አሣልፎ ለመስጠት ደባ የሸረበና ጉዳትም እያደረሰ  የቀጠለ በመሆኑ በእሱ በሚመራው መንግሥት ላይ ምንም ዓይነት ዕምነት የለንም፥ ሊኖረንም አይችልም። ዛሬ የኢሳይያስ መንግስት ለኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች ደጋፊ ለመምሰል አገራችንን ለረጅም ጊዜ ለማተራመስ ባለዉ ዕቅድ ባንድ ጎኑ ሽምቅ ተዋጊ ነን ባዮችን በተላላኪነት እያሰማራ በሌላ በኩል በፅኑ መሰረት የታነጸ የተቃዋሚዎች ህብረት እንዳይፈጠር የሚከሸፍበትን ስምሪት እያጠናከረ በምንም መልኩ ለኢትዮጵያውያን ዘላቂ መፍትሔ የሚፈልግ የተቃዋሚዎች ህብረት እንዳይፈጠር ሌት ተቀን ደፋ ቀና የሚልበት የእጅ አዙር ጫዋታዉን ቀጥሏል። ስለሆነም ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቆመናል የሚሉ ተቃዋሚ ድርጅቶችን በተመለከተ ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ ጉልህ የፈተና ወቅት ሆኗል ከምንም በላይ በራስ መተማመንና የሃገሪቱን ሉዓላዊነትና የሕዝቧን አንድነት መሰረት ባደረገ መርኅ ስር በመሰባሰብ በጋራ መስራት ማስፈለጉ የማያጠያይቅ ሆኗል ኢሕአፓ ዛሬም እንደትናንቱ ለጋራ ሃገራችን በጋራ ለመስራት እንነሳ የሚል ጥሪውን ከፍ አድርጎ ካሰማ ውሎ አድሯል ምላሹንም እየተጠባበቀ ነው
ለመሆኑ ሙሉ በሙሉ በሕወኃት/ኢሕአዴግ ቁጥጥር ስር የዋለው የኢትዮጵያ የወቅቱ ኢኮኖሚ ሁኔታ ምን ይመስላል? ለምላሹ በክፍል አራት የኢትዮጵያ ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታ ዝግጅታችን ለመገናኘት በቀጠሮ ብንለያይስ?